# ኢሕአፓ በኖርዌይ የተሳካ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄደ

የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባላት የተገኙበት ህዝባዊ ስብሰባ በኖርዌይ ኦስሎ ከተማ ተካሂደ።

በዚሁ ሰኔ 5 ቀን 2002 ዓ. ም. (ጁን 12 ቀን 2010) በተካሄደው ስብሰባ ላይ የድርጅቱ የበላይ አመራር አካል አቶ ኢያሱ አለማየሁ እና ዶ/ር ዘነበ ተሾመ የተገኙ ሲሆን ስለድርጅቱና ስለ ኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ሰፋ ያለ ማብራርያ ሰጥተዋል።



የወያኔን አገዛዝ አስመልክቶ በተለይ ከምርጫው ቧልት በኋላ ማንነቱ በጠራና ግልጽ በሆነ ሁኔታ እየተጋለጠ መምጣቱን የገለፁት አቶ ኢያሱ ትግሉ ከፊታችን የተደቀኑ በርካታ ችግሮችን መፍትሄ ለመስጠት በሚገባ ማየትና መመርመር አስፈላጊ መሆኑን ጫና ሰጥተው አብራርተዋል። ከዚህ አንጻር በቅርቡ ጎራ እያስለየ በማነታረክ ላይ የሚገኘው የአባይ ወንዝና እንዲሁም ለም መሬቶችን ለባዕዳን መቸርቸር እያስከተሉና ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳቶች  በአብነት ጠቅሰዋል። አያይዘውም ኢሕአፓ በቅርቡ ያቀረበውን የትብብር ውይይት ጥሪ መንፈሱንና ይዘቱን አስመልክቶም ሰፋ ያለ ማብራሪያና እንዲሁም ጥሪው ለምን በዋናነት  በሁለገብ የትግል ሥልት ወያኔን ከሥልጣን ለማስወገድ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ሀይሎችን እንደሚመለከትም ዘርዘር አድርገው አብራርተዋል።  ወቅቱ መሆኑንም አብክረው ገልፀዋል። አቶ ኢያሱ ቀጥለውም ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ካላት ተፈጥሮአዊ አቀማመጥና ወንዞች እስከዛሬ ድረስ የወያኔ መሬታችንን ለባዕዳን መስጠታና የአባይ ወንዝ ውዝግብ እንደ አብነት የሚጠቀስ መሆኑን ገልፀው የተቃዋሚው መፍረክረክ ግን ወደ መፍትሄ እንዳንሄድ ገደቦናል በማለት ገልፀዋል።



ዶ/ር ዘነበም በተጨማሪ ወያኔ ከውልደቱ ጀምሮ የሚከተለው ፖሊሲ አሁን ለሚገኝበት ፍጹማዊ አምባገነንነት በግዴታ ያደረሰው መሆኑን በስፋት ካብራሩ በኋላ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩባት የፖለቲካ ሥርአት ለመገንባት ሁኔታው በሚጠይቀው መልክ መደራጀትና መታገል እየታገሉም መጠናከር አስፈላጊ እንደሆነ ጠቁመዋል። ራሱን በሚገባ ያጠናከረና ያደራጀ ብቻ ለሕብረት እንቅስቃሴም ተገቢውን አስተዋጽዖ ሊያበረክት እንደሚችል አብራተዋል።







በዕለቱ ከስብሰባዉ ታዳሚዎች በትግል ሂደቱና በድርጅቱ ዙርያ በርካታ ግልፅና ዲሞክራሲያዊ አስተያየቶችና በተለይም በደርጅቶች የጋራ ትግል ላይ ያነጣጠሩ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበው ከመድረኩ ከድርጅቱ ቀደምት ታሪክ ጀምሮ ለጋራ ትግል ያደረገውን ጥረትና ወደፊትም በጋራ ለመሥራት ያስችል ዘንድ ስፊ የህብረት ተመክሮውንም ለማካፈል ለታዳሚው በስፋት ቀርቧል።



በትግል ሂደት ላይ ለተሰዉት፣ ደብዛቸው ለጠፋው  በአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት በማድረግ በተጀመረው በዚሁ ስብሰባ ላይ የድርጅቱ የኖርዌይ ክፍል ተወካይ አቶ ጌትነት ውብሸት ለዝግጅቱ ዕውን መሆን የጋራ ርብርቦሽ ያደረጉትን አባላትና ደጋፊዎቹን ከፍ ያለ ምስጋና ያቀረቡ ሲሆን በውይይቱ መካከል ወኔ ቀስቃሽና አስተማሪ የሆኑ ስነ-ግጥሞች በአቶ ቴዎድሮስ ቀርበዋል።



በመጨረሻም በወ/ት ማርታ በኢሕአፓ ኖርዌይ ሥም ለእንግዶቹ ስጦታ ቀርቦ የዝግጅቱ ፍጻሜ ሆኗል። ታዳሚውም በዝግጅቱ የረኩ መሆናቸውንና ወደፊትም የዚህ አይነት ዝግጅቶች እንዲቀጥሉ የተጠየቀ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።